# ሕዝቤን ልቀቅ !!

ሰዋስው ስለሺ

December 23, 2015

**«... እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ... ሕዝቤን ልቀቅ»**

ኦሪት ዘጸአት 8፣1

ፈሪሐ እግዚአብሔር የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንገቱን ደፍቶ ፣ በሚደርስበት መከራ ሁሉ፣ ጠግቦ በላዩ ላይ በሚየገሳው እና፣ ደርሶ የስራ መስክ በየቦታው የከፈተለት ይመስል «ሰርተህ አትበላም ወይ?» እያለ በላዩ ላይ በሚመጻደቀው መንገደኛ ላይ በደል ከመፈጸም ይልቅ፣ አንገቱን ደፍቶ፣ መናኛ ብጣሽ ጨርቅ መሬት ላይ አነጥፎ፣ «ስለ እግዚአብሔር የምበላው ያጣሁ የናንተው ቢጤ ነኝ ተመጽወቱኝ?» እያለ ድምፁን አሰምቶ ለመለመን እንኳዋን እፍረት ይዞት፣ ላላፊ ለአገደመው ሁሉ አንገቱን አቀርቅሮ እጁን እየዘረጋ ፣ ትርፍራፊ ተጥሎለት ጉሮሮውን እንዳያሙዋሽ እንኩዋ፣ የከተማዋን ገጽታ ያበላሻል ተብሎ በቆመጥ እና በሰደፍ እየተሳደደ፣ ለመለመን ያልቻለ፣ ስለ ችግሩ ለመጮህ ያልተፈቀደለት፣ ወገኑ ቢገደልበት ለማልቀስ ያልታደለው ሕዝቤ ፣ አይኑን ወደ ሰማይ አንጋጦ ዘወትር «አምላኬ ሆይ ለምን ረሳህኝ? «እያለ ለዘመናት የጮኀው የሰቆቃ ድምጽ የጸባኦትን በር ቀንና ሌሊት ያንኩዋኩዋል፡፡ የእግዚአብሔር አጆች ከሕዝባችን ጋር ሆነው ጣልቃ ገብተው መላ ካላመጡ በስተቀር ነገሮች እጅግ የከፋ አዝማሚያ ላይ እየመጡ መሆናቸውን በየቀኑ የምንሰማው መረጃዎች ይጠቁማሉ፣

በእርግጥ እምነት አለን የምንል ሰዎች እምነታችን እንደሚያዘው ለድሐ አደጉ፣ ለተራበው ለታረዘው፣ ለተገደለው፣ ለተሰደደው ... ወዘተ ሕዝብ፣ ሐይማኖታችን እንደሚያዘው ጮኀናል ወይ? ተሙዋግተንለታል ወይ? ምናልባትም ከእኔ በላይ ሐይማኖተኛ ለአሳር እያለ፣ ለቆመለት ቤተእምነት ቀኖና ወይም ጠበቃ ከመቆም ያላለፈ ስራ ያልሰራው ሐየማኖተኛ ነኝ ባይ ሁሉ ፣እስከዛሬ ዝም ማለታችን የምድራችንን ችግር ካባባሱት ነገሮች አንዱ እንደሚሆን አልጠራጠርም፡፡

በኖርዊጅያን ቁዋንቁዋ አንድ አባባል አለ «Den som tier han samtykker» ይላሉ ይህም ማለት አንድ ሰው ሲበደል እያየ ዝም የሚል ሌላ ሰው፣ ለበደሉ ተባባሪ ነው፣ በደሉ እንዲደረግ ፈቅዶ ተስማምቶአል ማለታቸው ነው፡፡ እኛም በደል እያየን እንዳላየ፣ እየሰማን እንዳልሰማ አስመስለን የህዝባችን ችግር ችላ ብለን፣ በተሸነተፕንባቸው የሐይማኖት ድርጅቶች ጎራ ውስጥ ያሉትን አመራር አባላት ላለማስቀየም ወይም በሐይማኖት ድርጅቱ ውስጥ ሐይማኖታዊ ሽፋን ተሰጥቶት ካደራጁን ማሕበራዊ መረብ (Networks) ውስጥ ያፈራናቸውን ወደጆች ላለማጣት እና ከዚህ ሕብረት ውስጥ ብውጣ፣ ልጆቼ ካደጉበት እና ጉዋደኛ ካፈሩበት ሕብረተሰብ ቢለዩ እንዴት አደርጋቸዋለሁ? እኔስ እንደገና አዳዲስ ጉዋደኛና አዲስ ሕብረት ለማፍራት እንዴት እችላለሁ? «ስለዚህ ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል «በሚል ምርጫ ላለመናገር እና ሳንወድ በግድ በሕሊና እስርቤት ውስጥ ተሸሽገን ያለንውን «የሐይማኖት ሰዎች» ቤት ይቁጠረው? የአምልኮ መልክ በሚመስል ግብዝነት፣ ትህተና በሚመስል ጭንብል ማስክ ራሳችንን ሸፍነን፣ ክርስቶስ በደሙ ነጻ ያወጣው ሕዝብ እንደገና በሰው ሰራሽ ህግና ሥርአት ባርነት ውስጥ ወድቆ ፣ የክርስትና እምነት መሰረት የሆነው ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚለው መርሖ ተሸሮ፣ ስለ ወገን መራብ፣ መታሰር፣ መሰደድ፣ መንገላታት መሙዋገት፣ ፖለቲካ ነው እንዳትነኩት ተብሎ ተነቀፈ፣ ምን አይነት የህሊና እስር ቤት ውስጥ መግባት ይሆን?

ከእነዚህ ሰዎች ጋር በግል ውይይት እንደተረዳሁት በልባቸው ስለ ሕዝባቸው ችግር ያስባሉ፣ በጉዋዳቸው ያለቅሳሉ፣ የተሰጣቸው መመሪያ ግን ከመፀለይ ውጭ ምን ማድረግ እንችላለን? ብለው እንዲያስቡ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየው ከመፀለይ በስተቀር ምንም እንዳንሰራ እና እንዳናስብ አድርጎ እግዚአብሔር እንደፈጠረን ሮበት አይነት ሰው ሆኖ ማሰብ ሲሆን፣ እጅግ ውብና ድንቅ አድርጎ፣ እንድናስብም፣ እንድንፀልይም፣ የፈጠራ ችሎታችንን ተጠቅመንም በተግባር ማድረግ የምንችለውን መልካም ነገር ሁሉ እንድንሰራ አድርጎ የፈጠረንን የፈጣሪያችንን የእጁን ስራዎች እና ፈጣሪያችንንም መናቅ እና ማቃለል ነው፡፡ ስለዚህ እስከዛሬ በሐይማኖት ስም በሕዝባችን ደም ለነገዱ እና እየነገዱ ላሉ ሁሉ እንደ ትውልድ እናት ያለኝ መልእክት እንደሚከተለው ነው!

«ቀኑ ሳይጨልምባችሁ ንስሐ ግቡና! ስለ ሕዝባችን መከራ ግድ ይበላችሁ! በተለይ በሐይማኖት እና በእግዚአበሔር ስም የምትነግዱ፣ የበግ ለምድ የለበሳችሁ ተኩላዎች! እናንተ የእፉኝት

ልጆች! «አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና «ገላትያ 6፣7 እግዚአብሔር ለክብሩ በተከላት ቤተ ክርስቲያን ላይ አትነግዱ! እስከዛሬ ድረስ በሐይማኖት ስም የነገዳችሁት እና የሰራችሁት ፖለቲካና «ቸርች ቸርች ጨዋታ» ይብቃችሁ! ሕዝቡ ስለ አገሩ ስለ ወገኑ እንዳይሰማ፣ በልጉዋም እንደተለበበ ፈረስ ወደ ቀኝም ወደ ግራም እንዳይመለከት እና ዘመኑንንም እንዳይዋጅ፣ እናንተ በየፖለቲካው ጎራ፣ ራሳችሁን በስውር አደራጅታችሁ፣ የፖለቲካ ስራችሁን እየሰራችሁ፣ መንጋውን «አገርህ በሰማይ ብቻ ነውና ስለምድርም ስለ ሕዝብህም አታሳብ» እያላችሁ የማያውቀውን የሰማዩን አገር ብቻ እንዲናፍቅ፣ ያላየውን እና ያላወቀውን እግዚአብሔር የሚያመልክ እንዲመስለው፣ የአምልኮ መልክ እያለበሳችሁት፣ በልማዳዊ እና በዘመናዊ የሐይማኖታዊ ልማድ ሥርአት ብቻ ስር እንዲቀመጥ አደንዝዛችሁ፣ በቅርቡ ያለው ወንድሙ ወይም እህቱ ችግር ግድ እንዳይለው የምታደርጉ ሁሉ ንስሐ ግቡ!

እናንተ ስተፈልጉ አውሮፓ፣ ስትፈልጉ፣ አፍሪካ፣ ስትፈልጉ አሜሪካና እስያ፣ ኢትዮጵያም ውስጥ ጭምር ከድሐው በተነጠቀው መሬት ላይ ንብረት እያከማቻችሁ እና በምድር ቤተመንግስታችሁን እየገነባችሁ፣ ለእናንተ አጎብድዶ ብቻ እንዲኖር ያደረጋችሁትን ምእመናን ስለ ምድር፣ ስለ አገሩ እና ስለወገኑ እንዳያስብ የእግዚአብሔርን ቃል እያጣመመቻሁ ታደነቁሩታላችሁ፣ እናንተ በአውሮፓ እና በአሜሪካ ተቀምጣችሁ ባገር ቤት ለጀመራችሁት የእርዳታ ፕሮጀክት ብቻ እንዲረዳላችሁ ፣ አድርጋችሁ ከመንግሥት ጋር ትወዳጁበታላችሁ! ለእናንተ የሚሰግዱ «እከክልኝ

ልከክልህ» አይነት ወዳጅ ዘመድ ታፈሩበታላችሁ! በውጭ ያለውን ሕዝብ፣ በየቤተ እምነታችሁ ባደራጃችሁት የቤት ሰሪ ማኅበር ከኢትዮጵያ ጋር ስላስተሳሰራችሁት፣ የሕዝብን በደል ቢናገር አገር ቤት ያፈራው ሐብት ወይም ቤት ይወረስበኛል በሚል ስጋት ምንም እንዳይናገር ለጎማችሁት፣ ከእናነተ ቤተ እምነት ውጭ ስለሆነው ስለ ገዛ ስጋ ዘመዱን እንኳዋን ግድ እንዳይለው ከዘረኝነት የከፋ የሐይማኖት ዘረኝነት ውስጥ ጨምራችሁ ታጠቡታላችሁ! አእምሮውን አቆሸሻችሁ ከእናንተ በላይ ጻድቅ እንደሌለ፣ ሌላውን ሰው አለማዊ፣ ሐጢያተኛ፣ ጠጪ፣ ሰካራም፣ አመንዝራ፣ እያላችሁ ስለ ሰው ልጅ ሐጢያት የሞተው የጌታችን እና የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ዋጋ አሳንሳችሁ፣ ለየጎሳችሁ እና ለየፖለቲካ ድርጅታችሁ አጀንዳ ማስፈጸሚያ፣ የክርስቶስን አካል ከፋፍላችሁ፣ ክርስቶስ ያልተጸየፈውን ይልቁንም ሐጢያተኛን ሁሉ ወደ ንሥሐ የጠራበትን ማንነት እየተጸየፋችሁ፣ የራሳችሁን ጽድቅ ቆልላችሁ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ደም እያጣጣላችሁ፣ ለተቀመጣችሁ ግብዞች እና ፈሪሳውያን ሐይማኖተኞች እና የሐይማኖት መሪዎች! እስከዛሬ ድረስ ጊዜ ለእናንተ አዘንብሎ በሐይማኖት ስም የፈለጋችሁን ስትሰሩ ቆይታችሁዋል አሁን ግን <u>በቃ! ሕዝቤን ልቀቁ እላችሁዋለሁ!</u> ንስሐ ግቡ! ወደ ወገኖቻችሁ፣ ወደ ጽድቅ ፈላጊዎች፣ ወደ እርቅ ፈላጊዎች፣ ታራቂ ወደ ሆነው፣ ይቅር ባይ ወደ ሆነው፣ ወደ ተበደለው፣ ወደ ደጉ ሕዝባችን ተጠጉ፣ አለያ ስለ ጻድቅ፣ ስለፍትሕ፣ ስለበደል በሚጮሁ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ላይ አፋችሁን አታላቁ!

«ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ተነሥቶ የሚጀመርበት ጊዜ ደርሶአልና፤ አስቀድሞም በእኛ የሚጀመር ከሆነ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን? «ተበሎ በ **1** ኛ የጴጥሮስ መልእክት **4**፣**17** ላይ እንደተጻፈ ንስሐ ግቡ! በሐይማኖት ስም የጠፈራችሁትን <u>ሕዝቤን ልቀቁ!</u> ትግላችን ዘረኝነትን አውጀ ሕዝባችንን በጦርነት፣ በረሐብ! በእርዛት፣ በእስራት፣ በስደት እና በመግደል ከሚያሰቃየው ዘረኛ እና ከሐዲ ሥርአት ጋር ብቻ ሳይሆን በሐይማኖት ስም እየነገዳችሁ ሕዘቡን ወይ ከመንግስት ጎን እንዲቆም አለያም ዝም እንዲል ተብትባችሁ ከያዛችሁት ከእናንተም ጋር ጭምር ነውና <u>ሕዝቤን ልቀቁ!</u> ሰው ስለ አገሩ ስለ ወገኑ፣ ሲቆረቆር ሐይማኖቱን ስቶ ፖለቲከኛ ሆነ ብላችሁ ከሕብረታችሁ ታገልሉታላችሁ፣ ሰው ሁሉ እንዲጠላው ዘመቻ ትከፍቱበታላችሁ፣ እጃችሁን ከጽድቅ እና ከፍርድ ተሙዋጋቾች ላይ አንሱ! እናነተ መስራት ካልፈገለጋችሁ በሚሰሩት ላይ አትዝመቱ! <u>ሕዝቤን ልቀቁ!</u> በመንግሥት ዙፋን እና በተለያየ አመራር ላይ ለተቀመጣችሁ፣ የሐይማኖት ካባ ለባሾች፣ በቤተመንግሥት ዙሪያ እንደ ጠንቁዋይ በሰበሰባችሁዋቸው ነብያት ተብዬ ደላዮች ትንቢት እየተመራችሁ፣ ከእግዚአብሔር ከመስማት ይልቅ በደህነነታችሁ መረጃ ላይ ብቻ የተደገፋችሁ፣ ስለ ሕዝቤ መከራ ግድ የሌላችሁ ሰዎች ሁሉ ንሰሐ ግቡ፣ <u>ሕዝቤንም ልቀቁ!</u> ሕዝቤን ባለፉት በርካታ አመታት በኤርትራ በረሐ፣ በትግራይ ተራራዎች፣ በመሐል አገር ወንዞች፣ በምዕራብ እና በምስራቅ ሜዳዎች፣ ላይ ስትጨርሱ ፣ ስታሰድዱ፣ ስትገድሉ፣ ስታጠፉ፣ ስታስሩ፣ የነበራችሁ ሹማምንት እና የነሱ ጋሻ ጃግሬዎች ሁሉ ንስሐ ግቡ፣ <u>ሕዝቤንም ልቀቁ!</u>

ይህን የምላችሁ ኢትዮጵያ በምትባል ምድር ባሉት ከሰማንያ በላይ ጎሳዎችን እናቶች የሰቆቃ ድምጽ በመወከል ነው፣ ምድሬ ፈውስ ያስፈልጋታል፣ የእምነት ቤቶች ፈውስ ያስፈልጋቸዋል፣ በትውልዱ መሐል ፈውስ ያስፈልጋል፣ በዘሮች መሐል ፈውስ ያስፈልጋል፣ በሕዝባችን መሐል ፈውስ ያስፈልጋል፣ በሕዝባችን መሐል እርቅ ያስፈልጋል፣ እናንተ ግን ይህ ሁሉ እንዳይሆን ከልክላችሁ፣ ሕዝቤንም ጠፍራችሁ የያዛችሁ! የጥላቻ ነቀርሳ በሽታ ምንጮች<u>ሕዝቤን ልቀቁ!</u> የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ምሑሩንም፣ የጦር መሪውንም፣ መሐንዲሱንም፣ ወታደሩንም፣ ሐኪሙንም ፣ ገበሬውንም፣ መምህሩንም፣ ነጋዴውንም፣ መሐይሙንም፣ ተማሪውንም፣ ካህኑንም፣ ሼኩንም፣ ክርስቲያኑንም፣ እስላሙንም፣ ሐይማኖት የሌለውንም ሁሉ የወለደችን፣ ኢትዮጵያዊ እናቶችን፣ እህቶችን፣ ሴቶች ልጆችን ሁሉ እየናቃችሁ፣ ሴቶችን በመሐበራዊ፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ትውልድን በማፍራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የምታደርገውን እናቶችን እና ሴቶችን እየረሳችሁና እየናቃችሁ፣ ለሕብረተሰቡ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ልታደርግ፣ ልትዳኝ፣ ልታስታርቅ፣ ተፈጥሮ ጥበብ ያደላትን እናት እና ሴት አያገለላችሁ ያላችሁ፣ ወንድሞቻችን ሁሉ፣ ባሕል የጣለብንን ሴት የመናቅ ነገራችሁን እግዚአብሔር ይፈውሳችሁ፣ እናንተም ንስሐ ግቡ፣ ወንድ ያለ ሴት፣ ሴትም ያለ ወንድ አይሆንም እና በጎናችሁ ያሉ እህቶቻችሁን አግዙአችሁ! ወንድምና እህቶች እጅ ለእጅ ተያያዙ! እያልኩ የምሰናበታችሁ የትውልድ እናትን የሰቆቃ ድምጽ የማስተጋባ ትውልደ ኢትዮጵያዊት እናት ነኝ ከወደ ኖርዌይ!

እግዚአብሔር ለኢትዮጵያና ለሕዝቡዋ ሁሉ ፈውስን ያምጣ ይባርከንም!

ሰዋስው ስለሺ ዮሐነሰን

**www.adonairapha.org**